# የጋራ ጋዜጣዊ መግለጫ

**የማህበራዊ ሚዲያዎች የንግድ ተቋማት ፣ የተቋማቱ ባለቤቶችን፣ በማህበራዊ ሚዲያ የሚሠራጩ መረጃዎች አዘጋጆችን፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን እና የመንግስት አካላትን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት አፋጣኝ በሆነ ሁኔታ በማህበራዊ ሚዲያ እየተስፋፋ የመጣውን የፆተኝነት እና የተሳሳቱ አሉታዊ መልዕክት ያላቸው ሴት ተኮር ይዘቶች እና ይዘቶቹን ተከትሎ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ ለማሳሰብ የተደረገ ጥሪ።**

እኛ ስማችን ከዚህ በታች የተገለጸው አገር በቀል የሲቪክ ማህበራት በማህበራዊ ድህረ ገጾች እና በመገናኛ ብዙሃን ላይ እጅግ እየተባባሰና አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰው ፆተኝነት እና ሴቶችን የሚያጥላሉ ይዘቶች ያላቸው መረጃዎች ስርጭት እና እንዲሁ ያሉ መረጃዎችን የሚያሰራጩ አካላት መበራከት እጅግ ያሳስበናል። እንዲህ ያሉ በሴቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩና ጎጂ የሆኑ መረጃዎች ሥርጭት እየተበራከተ መምጣት ፆታዊ እኩልነትን የሚጥሱ ከመሆናቸውም በላይ በሴቶች መብት መከበርና በማህበራዊ ደህንነት ላይም ከፍተኛ የሆነ ስጋትን የሚጥሉ ናቸው።

በአሁኑ ጊዜ ፆተኝነት እና የተሳሳቱ ሴቶችን የሚያጥላሉ ይዘቶች በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ በስፋት እየተሸራሸሩ ይገኛሉ። ፆተኝነት ማለት፡ በፆታ ላይ የተመሰረተ ጭፍንና የተዛባ ፍረጃ፣ የተሳሳተ አመለካከት ወይም መድልዎ፣ በተለይም በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውም አይነት አድልዎ ነው። የተሳሳቱ ሴት ጠል አመለካከቶች ማለት ዕይታዎች በሴቶች ላይ ያለን ጥላቻ እና የተያያዘ የተዛባ ምልከታን ያሳያል" ሁለቱም ቃላቶች ፆታን መሰረት ያደረጉ መድሎዎችን ያመለክታሉ። ይህም የሴቶችን ሰብአዊ መብቶች መጣስ በማስከተል እና በመጨረሻም በወንዶች እና በሴቶች መካከል የሃይል ሚዛን መዛባትን ይፈጥራል። ይህ ደግሞ ወንዶች የበላይ የሚሆኑበተትን እና ሴቶች ለመድልዎ ተጋላጭ የሚሆኑበትን ስርአት በማስከተል ሁከት እና ጥቃት የሞላበት ምህዳር ይፈጥራል።

ማኅበራዊ ሚዲያ በስፋት ግለሰቦች ሃሳባቸውን እንዲገልጹ እና የተለያዩ አመለካከቶችን እንዲለዋወጡ የሚያስችል ተፅዕኖ ፈጣሪ መድረክ መሆኑ የማይካድ ሀቅ ነው። ይሁን እንጂ ይህ መድረክ አንዳንዶች በብዛት የጾተኝነተ እና የተሳሳቱ ሴት ጠል አመለካከቶችን ለማስፋፋት ሲጠቀሙበት ማየት እጅግ የሚያሳዝን ተግባር ነው። በማህበራዊ ሚዲያዎችም ላይ ሆነ በእለት ተለት የህይወት እንቅስቃሴዎች ላይ በሴቶች እና ሴት ሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾቸ ላይ የሚደርስ የጥላቻ ንግግር፣ አድልዎ ወይም ጥቃትን አጥብቀን እናወግዛለን።
የዚህ ዓይነቱ ይዘት ያላቸው መልዕክቶች በስፋት መሠራጨት የሚያስከትለው መዘዝ በጣም ሰፊ ነው። ፆተኝነት እና የተሳሳቱ ሴት ጠል ይዘቶች ሴቶችን ዝቅ ከማድረግ ባለፈ በፆታ ላይ መሰረት ያደረጉ መድሎዎች፣ ጥቃት እና እኩልነት መጓደል መደበኛ ተግባራት እንዲሆኑ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። ይህ በቀጥታ የስርዓተ-ፆታ እኩልነትን ከማሳካት አንፃር የተጀመሩትን እንቅስቃሴዎች የሚያበላሽ እና በመላ ሀገሪቱ የሴቶችን ተሳትፎ የሚያደናቅፉ እና የሚገድቡ ጎጂ አመለካከቶችን ያስቀምጣል።

እነዚህን በፍጥነት እየተበራከቱ የሚገኙ ማህበራዊ የመረጃ ሥርጭቶችን በተመለከተ እኛ ስማችን ከዚህ በታች የተገለጸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሁሉም ባለድርሻ አካላትን፣ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮችን፣ የይዘት ፈጣሪዎችን፣ የሲቪክ ማህበራት እና የመንግስት ባለስልጣናት ይህን ጉዳይ በአስቸኳይ ለመቅረፍ እንዲተባበሩ ጥሪያችንን እናቀርባለን። የሚከተሉትን ድርጊቶች አፅንዖት እንሰጣለን፡-

1. የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች፡-
   - የማህበረሰብ መመሪያዎችን የሚጥሱ የፆተኝነት እና የተሳሳቱ ሴት ጠል ይዘቶችን በፍጥነት ለመለየት እና ለማስወገድ የማህበራዊ ሚዲያ የይዘት ማስተካከያ ዘዴዎችን ያጠናክሩ።
   - ተጠቃሚዎች አጸያፊ ይዘትን በቀላሉ ሪፖርት እንዲያደርጉ የሚያስችል ግልጽ የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴዎችን ያዘጋጁ።
   - ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የፆተኝነት እና የተሳሳቱ ሴት ጠል የማህበራዊ ሚዲያ ይዘት መስፋፋትን የሚከለክሉ አጠቃላይ ፖሊሲዎችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጁ።

2. የማህበራዊ ሚዲያ ይዘት ፈጣሪዎች፡-
- ለሚያዘጋጇቸው ይዘቶች ሀላፊነት እንዲውሰዱ እንዲሁም የእኩልነት፣ የመከባበር እና የአድሎአዊነት መርሆዎችን የሚያከብሩ መሆኑን ያረጋግጡ።
- ጎጂ የሥርዓተ-ፆታ አመለካከቶችን የሚፈታተኑ እና ሴቶችን የሚያበረታቱ አወንታዊ ትረካዎችን በንቃት ያስተዋውቁ። ይህንን ችግር በጋራ ለመፍታት በይዘት ፈጣሪ ማህበረሰብ ውስጥ ውይይትን እና መማርን በማጎልበት ራስን በመግዛት ውስጥ ይሳተፉ።

3. ኩባንያዎች
- የስርዓተ-ፆታ እኩልነትን ከግምት ውስጥ ያስገቡ ይዘቶች እና ማስታወቂያዎች በማስታወቂያ ኩባንያዎቻቸው አለመሰራጨታቸውን ያረጋግጡ።

4. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፡-
- ሁሉም የማህበራዊ ሚዲያ ይዘት ፈጣሪዎች እና የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎችን ስለፆተኝነት እና የተሳሳቱ ሴት ጠል የሆነ ይዘት ሊያስከትል የሚችለውን ተፅእኖ በማስተማር የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን ያካሂዱ።
- ለማህበራዊ ሚዲያ ይዘት ፈጣሪዎች የሚዲያ ክህሎት ማጎልበቻ ስልጠና እና ኃላፊነት የሚሰማውን፣ አካታች ይዘቶችን ለማዘጋጀት፣ ሂሳዊ አስተሳሰብን እንዲያዳብሩ ለመርዳት ስልጠና እና ግብዓቶችን ያቅርቡ።

5. ለመንግስት ባለስልጣናት፡-
- በማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ የጥላቻ ንግግርን፣ ፆተኝነትን እና የተሳሳቱ ሴት ጠል ይዘትን የሚከለክሉ ህግጋቶችን ያስፈጽሙ እንዲሁም መረጃዎችን ያጋሩ ።
- በበይነ መረብ የሚፈጠሩ ስርዓተ-ፆታ ላይ መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን እና መድሎዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚፈቱ የአሠራር ስልቶችን እና ፖሊሲዎችን ለማዘጋጀት በሚዲያ ተቋማት፣ በማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች እና በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መካከል ትብብርን ያሳድጉ።
- በይነ መረብ መሰረት ያደረጉ ፆታዊ ጥቃቶች እና የጥላቻ ንግግሮችን በተመለከተ ትርጉም ለመስጠት፣ ለማመልከት፣ ለመፍታና እርምጃ ለመውሰድ ደንቦችን ያዘጋጁ።

ለእኩልነት እና ለፍትህ ቁርጠኛ የሆንን ድርጅቶች እንደመሆናችን መጠን፣ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጠሩ ያሉ የፆተኝነት እና የተሳሳቱ ሴት ጠል ይዘቶችን እና የይዘት ፈጣሪዎችን ለመዋጋት ለሚደረገው ጥረት ድጋፍ እናደርጋለን። የሁሉንም መብት እና ክብር የሚያከብር ከማንኛውም ጥቃት ነፃ የሆነ ምቹ አካባቢ ለመፍጠር ሁሉም ግለሰቦች እና አካላት ንቁ አስተዋጾ እንዲያደርጉ እናሳስባለን። በጋራ ሴቶች በነጻነት የሚሳተፉበት፣ እኩል እድሎችን የሚያገኙበት እና አድልዎ እና ጥቃትን ሳይፈሩ የሚኖሩበትን ማህበረሰብ መገንባት እንችላለን።

**ፈራሚ ድርጅቶች**:
1. የኢትዮጲያ ሴት ሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች ጥምረት
2. የኢትዮጲያ ሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች ማእከል
3. የምብቶች እና የዴሞክራሲ ዕድግት ማእከል
4. የኢትዮጲያ ሴቶች መብቶች ተሟጋቾች
5. ሴታዊት
6. የኢትዮጲያ መገናኛ ብዙሃን ባልሙያ ሴቶች ማህበር
7. የኢትዮጲያ ሴት አካል ጉዳተኞች ማህበር
8. አዲስ ፓወር ሀውስ
9. ትምራን
10. ስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጲያ
11. የኢትዮጲያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር
12. የኢትዮጲያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት